# የግለሰቦችን ስም በማጠልሸት የህብረተሰቡ መሰረታዊ ችግሮች መፍትሄ ያገኙ ይሆን?

**እውነቱ ዘለቀ 12-15-16**

ሰላም ወርቅ ሁሉአገር የተባለ ጸሀፊ የአቶ ገዱ አንዳርጋቸውንና ተከታዮቻቸውን ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ችግር አጋለጥሁ በሚል ሽፋን እጅግ ወገናዊና በጥላቻ ላይ የተመሰረቱ ሁለት መጣጥፎች በአይጋ ፎረም ድረ-ገጽ ላይ በተከታታይ እንዲወጡ ማድረጉ ይታወሳል፡፡ የመጀመሪያው ጽሁፍ የወጣው ቀደም ብሎ የነበረ ሲሆን ሁለተኛው ጸሁፍ ግን በቅርቡ ማለትም ሀምሌ 2008 ዓ.ም (እአአ 08/08/2016) ላይ ነውና የወጣው እሱን እንደ መነሻ በማድረግ በተመጠነ መልኩም ቢሆን ተያያዥ በሆኑ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ትንሽ ልበል፡፡

ጸሀፊው ታዓማኒነት ለማግኘትና ይመለከተኛ ለማለት ይመስላል ጎንደር ተወልጄ ያደግሁ ጎንደሬ ነኝ በማለት አንባቢን ለማሳሳት ይሞክር እንጂ በአንደበቱ ወጥተው ጽሁፍ ላይ የሰፈሩት ቃላትና ሀረጋት ግን ጎንደር ተወልዶ ያደገና በአማርኛ ቋንቋ አፉን የፈታ ሰው ሊጠቀምባቸው የማይችላቸውን በእጅጉ የተወለጋገዱ የአማርኛ ቃላትን ደጋግሞ ስራ ላይ ሲያውል ተስተውሏል፡፡ በአብዛኛው የሚጠቀምባቸው ሀረጋትም ሆኑ ቃላት ሲታዩ ደግሞ አፉን በአማርኛ ቋንቋ ሳይሆን በትግርኛ የፈታና አብዛኛውን ጊዜም የትግርኛ ቋንቋን ሲጠቀም የኖረ መሆኑን የሚያረጋግጡ ሲሆን በአማራ ክልል ነዋሪነት በተለይም ጎንደሬነት ስም የክልሉ መሪዎች በተለይም የአቶ ገዱ አንዳርጋቸውንና ተከታዮቻቸውን ስም ለማጥፋት ሆን ብሎ የተነሳ እንደሆነ በግልጽ ያሳያል፡፡

ጸሀፊው በአማራ ክልል ነዋሪነት ወይም ጎንደሬነት ስም ከመነገድ ይልቅ ያነሳው ሀሳብ ትክክለኛና በማስረጃ የተደገፈ እስከሆነ ድረስ የእሱ አማራ አለመሆን ወይም ትግሬ መሆን ምን አሳሰበው? ወይስ የትግራይ ብሔር አባል መሆኑ በግልጽ ከታወቀ የአማራ ተወላጅ አንባቢ ላይቀበለኝ ይችላል ብሎ ስለሰጋ ይሆን? እኔ የዚህ አይነቱ የተሳሳተ አቀራረብ አደገኛ ከመሆኑም በላይ ማንኛውም ዜጋ በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ግለሰብም ሆነ ቡድን ላይ በያገባኛል ስሜት በአዎንታም ሆነ በአሉታ ሀሳብ እንዳይሰጥ የሚያደርግ ከመሆኑም

በላይ በጠባብ ብሔረተኝነት ታጥረን እንድንቀር የሚያደርግ አደገኛ አስተሳሰብ ስለሆነ ለሀገራችን ህዝቦችም ሆነ በስራ ላይ ለሚገኙ ፖለቲከኞች/አስተዳዳሪዎች አይጠቅምም ብየ አምናለሁ፡፡

በእርግጥ አቶ ገዱና ተከታዮቻቸው የአጠቃላዩ የሀገራችን መንግስት መሰረታዊ ችግሮች በተለይም በህወሀት/ኢህአዴግ የሚመራው የኢፌዴሪ መንግስት መሪዎች ብልሽት እንደ አንድ መገለጫ በመሆኑ እነዚህ ግለሰቦች ላይ ብቻ አተኩሮ እወነተኛም ይሁን በሀሰት የተቀነባበረ ሂስ ማቅረብ መሰረታዊውን የሀገራችንን ችግር ይፈታዋል የሚል አስተሳሰብ መያዝ በራሱ ችግር ያለበት ይመስለኛል፡፡ ከዘም አልፎ ጸሀፊው በ1997 ዓ.ም የቅንጅት ደጋፊ እንደነበር በጽሁፉ ላይ ሳያፍርና ሳይፈራ ገልጧል፣ እሰየው በአንድ ወቅት ተቃዋሚ የነበረ ሰው በሌላ ወቅት ደጋፊ የማይሆንበት ምንም አጋጣሚ የለምና አሳማኝ ምክንያት ከተገኘ አቋሙን መለወጡ ብዙም የሚያስገርም ላይሆን ይችላል፡፡ ሆኖም አንዳንድ ሰዎች እንደሚያደርጉት ለስልጣን፣ ለትምህርት አሊያም የተሻለ የቢዝነስ ዕድል ተጠቃሚ ለመሆን ስፈለገ በማስመሰል የገኘው ፓርቲ ህወሀት/ኢህአዴግ ደጋፊ ሆኖ እንዳይሆን ስጋት አለኝ፡፡

አቀራረቡም ወቅታዊ ሁኔታውን በመጠቀም የትግራዮችን በአጠቃላይና የህወሀት አባላትና ደጋፊዎችን በተለይ ቀልብ ለመሳብ የተደረገ ጥረት አሊያም በውስጡ እያሳደገ የመጣውን የቆየ ቂምና ጥላቻ በብአዴን መሪዎች በአጠቃላይና በገዱ አዳርጋቸው ላይ በተለይ ለመወጣት ፈልጎ ሊሆን እንደሚችል መገመቱ ስህተት አይሆንም፡፡ ምክንያቱም እውነተኛ የቅንጅት ደጋፊ ከነበረ በአንድ ጊዜ መቶ ሰማኒያ ዲግሪ ተገልብጦ “ህገ-መንግስታችንና ድርጅታችን ኢህአዴግ ታዕምር የሰራና እየሰራ ያለ ድርጅት ነው” ብሎ በድፍረት ለመጻፍም ሆነ በአደባባይ ለመናገር የሚያስችል ሞራልስ ከየት አገኘ ያሰኛልና ነው፡፡

ከላይ በአጭሩ ለመግለጽ እንደሞከርሁት በአንድ ወቅት ተሳስቶም ይሁን ከልቡ አምኖበት የቅንጅት አባል የሆነ ሰው አሁን ላይ ስህተቱን አርሞ ወይም ቀደም ሲል የነበረው ግምገማ ትክክል እንዳልነበረ ተገንዝቦ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ከሆኑት ውስጥ ወደ አንደኛው ጎራ ሊቀላቀል ይችላል፣ ሆኖም በአንድ ጊዜ ከመምህሩ ደቀ መዝሙሩ ለመሆን ግን እውቀቱም ሆነ የሞራል ብቃቱ ያን ያህል የሚፈቅድለት አይመስለኝም፡፡ ከዛም አልፎ በመጣጥፉ ውስጥ ስለ አማራና ኦሮሚያ ክልል አመራሮች የአስተዳደር ብልሽትና ሙስና ብዙ ነገር ሲያወራ ስለ ትግራይ ክልል አመራርም ሆነ ስለህወሀት ጸረ-ዴሞክራሲያዊነት

አንድም ነገር ለማለት አለመድፈሩ በራሱ የዚህን ሰውየ ማንነትና አላማ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡

በሌላ አገላለጽ ይህ ግለሰብ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ህወሀትና አንዳንድ ወግ አጥባቂ የሆኑ የትግራይ ተወላጆች በአቶ ገዱ አንዳርጋቸውና ተከታዮቻቸው አመራር ላይ እያሳደጉ የመጡትን የጥላቻ ስሜት መነሻ በማድረግ አቶ ገዱ በክልላቸው ሰዎችም እንዲህ ይባላሉ ለማስባል ተፈልጎ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በቅርቡ በባህር ዳር ከተማ የተካሄደው የአማራ ክልል ም/ቤት ጉባኤ በአቶ ገዱ አንዳርጋቸው አመራር ላይ ያለውን እምነት በድጋሜ አረጋግጦ እሳቸው ያቀረቧቸውን አዳዲስ የካቢኔ አባላት ተቀብሎ ያለምንም ተቃውሞ ማጽደቁ እውነታው ከህወሀት ሰዎችም ሆነ ጽሀፊው ሀሳብ ተቃራኒ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በእርግጥ ባለፈው አመት ከቅማንት ህዝብ የማንነት ጥያቄ በወቅቱ ምላሽ አለማግኘት እንዲሁም ለጥያቄው የተሸራረፈ ምላሽ አሰጣጥና ያልተገባ አያያዝ ጋር ተያይዞ በአጠቃላይም በክልሉ ውስጥ የሰፈነው የመልካም አስተዳደር ችግር በጊዜ አለመቀረፍ ምክንያት በተቀሰቀሰው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ሳቢያ በክልሉ የጸጥታ ሀይሎችና በቅማንት ብሔረሰብ አባላት መካከል ያልተፈለገ ግጭት ተከስቶ በመቶዎች የሚቆጠሩ የአካባቢው ነዋሪዎች በተለይም የቅማንት ብሔረሰብ አባላት ሲገደሉ በርካታ የህዝብና የመንግስት ንብረት ወድሟል፡፡

በዚህም ምክንያት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በሰሜን ጎንደር ዞን ጭልጋና ላይ አርማጭሆ አካባቢዎች ውስጥ አለመረጋጋት ሰፍኖ ቆይቷል፡፡ ከዛም ባሻገር ከወልቃይት ህዝብ የአማራ ማንነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የፌዴራል የጸጥታ ሀይሎች ኮሎኔል ደመቀ ዘውዱንና ከእሱ ጋር ይሰሩ የነበሩ የወልቃይት የአማራ ማንነት አስመላሽ ኮሚቴ አባላትን የአማራ ክልል መንግስት የስራ ሀላፊዎችም ሆኑ የከተማው የፖሊስ ሀይል ሳያውቅ ጎንደር ከተማ ውስጥ በመግባት በቁጥጥር ስር ለማድረግ በተወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ ተኩስ ተከፍቶ በአስሮች የሚቆጠሩ የጸጥታ ሀይሉ አባላት ሲገደሉ የበርካታ ሲቪሎች ህይወትም ጠፍቷል፡፡

በዚህም ምክንያት የጎንደር ከተማና የአካባቢው ህዝብ የተደፈርን አይነት ስሜት ውስጥ ገብቶ በመንግስት ሀይሎችና ደጋፊዎቹ በተለይም በህወሀት/ኢህአዴግ የማን አለብኝነት እርምጃ ላይ የተቃውሞ ድምጹን በመጀመሪያ በሰላማዊ መንገድ ለማሰማት ጥረት አደረገ፡፡ ሆኖም የመንግሰትና የደጋፊዎቹ ምላሽ የተገላቢጦሹ ሆኖ ሲያገኘው ከህምሌ

አምስት 2008 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሀይል እርምጃ ውስጥ በመግባት ጉልበተኛን በጉልበት ለመመከት ሞከረ፡ በዚህም ሳቢያ በርካታ የሰው ህይወት ጠፋ፣ እጅግ ቁጥሩ የበዛ የመንግስትና የህዝብ ብሎም የግለሰቦች ሀብትና ንብረት ወደመ፣ በሽዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆችም ያለ አግባብ ተፈናቀሉ፡፡

ይህ ሁኔታ እጅግ አሳዛኝና በፍጹም ሊደገም የማይገባው በአጠቃላይም ተቀባይነት የሌለው ድርጊት ቢሆንም የህወሀት መሪዎችና ወግ አጥባቂ ደጋፊዎቹ እንደሚያስወሩት ጥቃቱ በትግራይ ተወላጆች ላይ ብቻ ያነጣጠረ እንዳልነበር በርካታ ማስረጃዎችን በማቅረብ የተሳሳተውን ሀሳብ መሞገት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው እኔ እስከማውቀው ድረስ ጎንደር ከተማ ውሰጥ ብቻ በአስር ሽዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆች እንደሚገኙ ቢታወቅም የተፈናቀሉት ግን በመቶዎች እንኳ አይሞሉም፡፡

እነሱም ቢሆኑ በአሜሪካ ድምጽ ጋዜጠኞች አማካኝነት ቃለ ምልልስ ሲደረግላቸው ከሰጡት መልስ መረዳት እንደሚቻለው አንዳንድ ግለሰቦች ስላስፈራሯቸው መሆኑን ከማረጋገጣቸውም በላይ ሀብትና ንብረታቸውን ይዘው ወይም ለአስተማማኝ ጠባቂ ሰጥተው በተረጋጋ ሁኔታ ከፊሎቹ በአውሮፕላን ሌሎቹ ደግሞ አስቀድሞ በተዘጋጀ አውቶብስ ያለምንም እንግልት ወደ መቀሌ ማቅናታቸውን ታዘዝበናል፡፡

እውነት ነው በቋራ ወረዳ ሽንፋ ከተማና በአብዛኛው የገጠር አካባቢዎች ይኖሩ የነበሩ የትግራይ ተወላጆች በእግራቸው በመኪና በሱዳን አድርገው ሁመራ መግባታቸውን ሰምተናል፣ ይህም ቢሆን የአቶ ገዱ አንዳርጋቸውንና በብአዴን የሚመራውን የክልሉን አመራር ለማሳጣት ሆን ተብሎ የህወሀት አባላት በሆኑ የደህንነቱ ሰዎችና ፖለቲከኞች አማካኝነት አስቀድሞ የተወጠነ ሴራ ነው የሚሉ መረጃዎች እየወጡበት ይገኛል፡፡

ለዚህም ይመስለኛል በጊዜው በአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ጣቢያ ባለደርባና መቀሌ ሆኖ በሚዘግበው ግርማይ ገብሩ አማካኝነት ለአንዳንዶቹ ተፈናቃይ ተብየዎች መቀሌ ሲገቡ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ በአንዳንድ ግለሰቦች አማካኝነት የማስፈራራት ድርጊት ስለተፈጸመብን ነው ወደዚህ የመጣነው በማለት መልስ የሰጡት፡፡ አንዷ ሞልቃቃማ አንድ ወጣት መጥቶ ወዮልሽ አጠፋሻለሁ ብሎ ስላስፈራራኝ ወዲያውኑ ወደ አዲስ አበባ ከሄድሁ በኋላ ወደ መቀሌ በአውሮፕላን መጣሁ ስትል ኩሀ በሚገኘው የአሉላ አባነጋ አውሮፕላን ማረፊያ ላይ በኩራት መንፈስ ውስጥ ሆና ምላሽ ሰጠች፡፡

ከዛም ባሻገር የአማራ ክልል መንግስት ቃል አቀባይ የሆኑት አቶ ንጉሱ ጥላሁንም የአሜሪካ ድምጽ የአማርኛው አገልግሎት ጋዜጠኛ ላቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ በአሀዝ አስደግፈው እንዳረጋገጡት ከሆነ በጊዜው ጎንደር ከተማ ውስጥ በተፈጠረው ግርግር ብቻ ንብረታቸው ከወደመባቸውና ከተሰባበረባቸው 130 የከተማው ነዋሪዎች ውስጥ 30ዎቹ ብቻ ናቸው የትግራይ ተወላጆች ሆነው የተገኙት፡፡

የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል እንደሚባለው ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው በተወሰኑ የትግራይ ተወላጆች ላይ የዛቱ ወይም የማስፈራራት ድርጊት የፈጸሙ ግለሰቦች ወይም የከተማው ነዋሪዎች የሉም የሚል ጭፍን የሆነ የመከራከሪያ ሀሳብም የለኝም፡፡ ይህም የሆነው ግን አብዛኛዎቹ የትግራይ ተወላጆች የስርአቱ ደጋፊዎች ወይም አባላት በመሆን በንቃት ሲሳተፉ ከመመልከታቸው ጋር ተያይዞ በጥላቻ ስሜት የተፈጸመ ስሜታዊ ድርጊት እንጂ በሁሉም የትግራይ ተወላጆች ላይ ያነጣጠረና በዘር ላይ የተመሰረተ ዘመቻ እንዳልሆነ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ የሚገርመው ነገር የንብረት መውደሙም ሆነ የማሰፈራራቱ ድርጊት በትግራይ ተወላጆች ላይ ብቻ ሳይሆን የተፈጸመው በአማራና በቅማንት ብሔረሰብ አባላት ላይም ጭምር መሆኑ የሚታወቅ ሆኖ ሳለ በእጅጉ ተጋኖ የተወራለትና የተዘገበለት ብሎም የሀብት ማሰባሰብ ተግባር የተከናወነለት ግን የተወሰኑ የትግራይ ተወላጆች ንብረት መውደምና መፈናቀል ነው፡፡

በእውነት ለመናገር በሀገራችን አስተዋይ ልቦና ቢኖርና ፍትሀዊ የሆነ ፍርድ ሊሰጥ የሚችል የፖለቲካ ምህዳር ቢሰፍን ኖሮ በከፋ መልኩ የህይወት መጥፋት አደጋ የደረሰውም ሆነ በአካባቢው የሰላም መታጣት በእጅጉ የጎዳቸው የትግራይ ተወላጆችን ሳይሆን የአማራና የቅማንት ብሔረሰብ አባላትን መሆኑ ሊታወቅ በተገባ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ በአማሮችና ቅማንቶች ላይ የደረሰው ተደራራቢ በደል፣ የህይወት መጥፋትና የንብረት ውድመት ወደ ጎን ተብሎ ሁሉም ነገር በተወሰኑ የትግራይ ተወላጆች ላይ የብአዴን አባላትና የቀበሌ አመራሮችን ጨምሮ በአንዳንድ የጥፋት መልክተኛ በሆኑ ግለሰቦችና ቡድኖች አማካኝነት በተፈጸመው የንብረት ማውደምና የመፈናቀል ድርጊት ላይ እንዲያተኩር ተደረገ፡፡

ይህም የሆነበት ምክንያት ደግሞ ግልጽ ነው፣ ይኸውም ባለፉት ሀያ አምስት አመታት በሀገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በየትኛውም ክልል የህወሀትና የትግራይ ተወላጆች ተሰሚነትና

የበላይነት መንፈስ በእጅጉ ሰፍኖ ከመቆየቱ ጋር ተያይዞ በዚህ ወቅት እንዴት ተደፈርን የሚል የቁጣ ስሜት ስለቀሰቀሰ እንደሆነ መገመት አይከብድም፡፡ አማሮቹና ቅማንቶቹ በትግራይ ተወላጆች ላይ ከተፈጸመው በላይ በእናት ክልላው ውስጥ ያን ያህል ግፍ ቢደርስባቸውም ለዘመናት የኖሩበትን የትውልድ አካበቢያቸውን ለቀው ወደ የትም መሄጃ ስለሌላቸው ከዚህም የባሰ የከፋ እንግልትና ችግር እየገጠማቸውም ጭምር አርፈው ለመቀመጥ ተደዱ፡፡

ተጠቃሎ ሲታይ በአማራ ክልል ውስጥ ከሰላሳ እስከ አርባ ሽህ ሚገመት ቁጥር ያላቸው የትግራይ ተወላጆች የሚኖሩ ሲሆን (አብዛኛዎቹ ጎንደር ከተማና በአካባቢው ነው የሚገኙት፣ አንዳንዶቹ ደግሞ አሁንም ድረስ የቢሮና የመምሪያ ሀላፊ በመሆን በመስራት ላይ የሚገኙ አሉ) ተፈናቀሉ የተባሉት ግን በትግራይ ክልል መንግስት በቀረበው ሪፖርት መሰረት ከአምስት ሽህ አይበልጡም፡፡

ይህም ቢሆን ተገቢ ነው የሚል የመከራከሪያ ሀሳብ የለኝም፡፡ ሆኖም እውነታው ተጋኖ የሚነገርለትን ያህል ካለመሆኑም በላይ ቀደም ሲል በአርባጉጉና በመሳሰሉት የኦሮሚያ አካባቢዎች የተፈጸመውን ግፍና በደል ትተን ባለፉት አስራ አምስት አመታት ብቻ በአስር ሽዎች የሚቆጠሩ አማሮች ከኦሮሚያ ክልል በተለይም ምስራቅ ወለጋ አካባቢ፣ ደቡብ ክልል ጉራፈርዳ ወረዳ ውስጥ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ለዘመናት ይኖሩ የነበሩ አማሮች ንብረታቸው ሜዳ ላይ ተበትኖና ወድሞ፣ ቤታቸው ፈርሶ የተወሰኑት ደግሞ አካላቸው ጎድሎና ህይወታቸው ጠፍቶ በህይወት የተረፉት በግፍ ሲፈናቀሉ የአማራ ክልል መሪዎችን ጨምሮ አንድም የክልል መንግስት ወይም የፌዴራል ባለስልጣን ድምጹን ባላሰማበት ሁኔታ አሁን ምን አዲስ ነገር ተገኝና ነው የኢትዮጵያ ሶማሊና የአፋር ክልል መንግስታት መሪዎች ውስን የሆነውን በጀታቸውን አጥፈው እያንዳንዳቸው የአስር ሚሊዮን ብር ለመስጠት ቃል መግባታቸውን በሚዲያ ሲናገሩ የቀደማቸው ሰው ያልተገኘውና ቀጥለውም ቼኩን በማስያዝ የሀገር ሽማግሌዎችን በሩጫ ወደ መቀሌ በመላክ አይዟችሁ ከጎናችሁ ነን ያሉት?

እጅግ የሚያሳዝነው ሁኔታ ደግሞ ከአመታት በፊት የአማራ ክልልን ወክለው የመጡት አንዲት የፓርላማ አባል በአማራ ተወላጆች ላይ በደቡብና በኦሮሚያ ክልል ውስጥ እየተፈጸመ ያለው የማፈናቀል ድርጊት ያውም በክልል መንግስታት መሪዎች ትዕዛዝና ዕውቅና ተገቢ ስላልሆነ በፌዴራል መንግስት አማካኝነት ሀይ ሊባል አይገባውም ወይ?

ብለው ለቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ጥያቄ ሲያቀረቡ አማሮች እኮ የተፈናቀሉት ደን ስለጨፈጨፉና ምስራቅ ጎጃምን ደቡብ ክልል ውስጥ ሊመሰርቱ ጥረት ስላደረጉ ነው በሚል መልኩ በምጸት የታጀበ ምላሽ በመስጠት ነበር በቁስላቸው ላይ እንጨት የመስደድ ያህል በሚቆጠር አኳኋን የችግሩን ሁኔታ ለማቃለል የሞከሩት፡፡

የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ ታዲያ ደን የጨፈጨፈ ግለሰብ ወይም ቡድን በአገሪቱ የህግ አግባብ መሰረት በወንጀል ተከሶ ሊቀጣ ይገባዋል እንጂ ከሚኖርበት አካባቢ በጅምላ እንዲፈናቀል ይደረጋል እንዴ በሚል መልኩ ሊቀርብ ለሚችለው ጥያቄ የረባ መልስ እንኳ አላዘጋጁም ነበር፡፡ ይህም ሆኖ በዚህ አጋጣሚ እጅግ የተጋነነና ለፖለቲካ ፍጆታነት ለማዋል በተሰራው ስራ ሳቢያ አጋር ለማሰባሰብ ጥረት የተደረገበት እርምጃ መሆኑ ተገቢነቱ ላይ አሉታዊ የሆነ ጥላ እንዲያጠላበት ያደረገ ቢሆንም ከአማራ ክልል ለተፈናቀሉት የትግራይ ተወላጆች የትግራይ ክልል መንግስት ፈጥኖ የወሰደው የአለሁላችሁ እርምጃና ራሱን የቻለ ጊዜያዊ ኮሚቴ ሳይቀር በማቋቋም ሀብት በማሰባሰብ ጭምር ተፈናቃዮችን ለመርዳት ያደረገው ጥረት በአርአያነት ሊታይ የሚገባውና በእጅጉም የሚደነቅ በመሆኑ ለሌሎች የክልል መንግስታት በአጠቃላይና ለአማራ ክልል መንግስት የስራ ሀላፊዎችና ለገዥው ፓርቲ ብአደን መሪዎች ደግሞ በተለይ እጅግ ጠቃሚ የሆነና አይረሴ ትምህርት ሰጥቶ ያለፈ ክስተት ስለሆነ ሊበረታታ ይገባዋል ባይ ነኝ፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ከላይ በምሳሌነት የተጠቀሱት ችግሮ ሊፈቱ የሚችሉት ሁሉን አቀፍ በሆነ ጥልቅ ተሀድሶና አድማሰ ሰፊ እይታ እንጂ ግለሰቦችን በተለይም የመንግስትንም ሆነ የህዝብን ሀላፊነት ይዘው አቅማቸው በፈቀደው መጠን የሚሰሩትን መሪዎች ወይም ቡድኖች ስም ጥላሸት በመቀባት ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ጊዜ ያለፈበት ኋላቀር ስልት እንደሆነ ግንዛቤ ቢያዝበት መልካም ይመስለኛል፡፡

ከሁሉም በላይ ግን የእኔ አውቅልህ አለሁ አቀራረብን ትተን ባለቤቱ ለሆኑት ለአማራ ክልል ህዝቦችና ለመላው የብአዴን አባላት ብንተወው የሚሻል እንደሆነ ሳንወድ በግድም ቢሆን አምነን ብንቀበል መልካም እንደሆነ ማረጋገጥ እፈልጋለሁ፣ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርሁት በተግባር የታየውም ይኸው ይመስለኛል፡፡ ጸሀፊው ጎንደር ከተማም ሆነ በአካባቢው ተወልዶ ያደገና የአፍ መፍቻ ቋንቋውም አማርኛ እንዳልሆነ፣ እንዲሁም እሱ ደጋግሞ ክልላችን በማለት አንባቢን ለማታለል እንደሞከረው የአማራ ክልል ተወላጅና

ጎንደሬ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ለሚፈልግ ሰው ቀጥለው በምሳሌነት በቀረቡት የቃላት አጠቃቀሙን በቀላሉ መመልከት ይችላል፡

እሰማለሁ ለማለት እሰማሎህ፣

እታዘባለሁ ለማለት እታዘባሎህ፣

አያለሁ ለማለት አያሎህ፣

እጠብቃለሁ ለማለት እጠብቃሎህ፣

አውቃለሁ ለማለት አውቃሎህ፣

የሚሉት አባባሎች ሰውየው በእርግጥም ማን እንደሆነና ምን አይነት ተልዕኮ ይዞ እንደተነሳ በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዚህ አይነት ፍጹም ወገንተኛና የተሳሳተ አቀራረብ ደግሞ ለህወሀትም ሆነ ለትግራይ ህዝብ አንድም ፋይዳ ሊያስገኝለት የሚችል አይመስለኝምና ለወደፊቱ ባይደገም ተገቢ ነው እላለሁ፣ ስለሆነም አንድ ሰው ሌላኛውን ሰው በተለይም የህዝብና መንግስት ሀላፊነትን ተሸክሞ በሚገኝ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ አስተያየት ለመስጠት ስንሞክር በአንድ በኩል ከስሜት፣ ከጥላቻና ወገናዊነት በራቀ መልኩ በሌላ በኩል የራስን ትክክለኛ ማንነት ሳይደብቁ ጉዳዩ ያገባኛል ብሎ ሀሳብን መግለጽ መቻል በእርግጥም አስተዋይነት የሚስተዋልበት አቀራረብ ከመሆኑም ባሻገር ለሁሉም ወገን አስተማሪ የመሆን ዕድሉ ሰፊ ነውና በዚህ መልኩ ቢታሰብ መልካም ነው እላለሁ፡፡

ቸር ይግጠመን!